**"እግዚአብሔርስ፡ ገሃደ ይመጽእ!**
**ወአምላክነሂ፡ ኢያረምም!**
**እሳት ይነድድ ቅድሜሁ!"**

\+ + +

**"ቸሩ ፈጣሪያችንና አምላካችን፥**
**ካህናችንና ንጉሣችን እግዚአብሔር፡**
**ስለአባትነት ዳኝነቱ፡ ዝም እንዳለ አይቀርም!**
**በፊቱ፡ እሳት እየነደደ፡ በግልጽ ይመጣል!"**

\+ + +

እንዲህ የተባለለት፡ ራሱ የፍጥረቱ አስገኚና መጋቢው መሪ፡ በትስብእት ቤዛነቱ፡ ፍጡሩን ሊያድን፥ በአብነት ቃሉም ሊያስተምረው፡ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሣለ፡ **"እሳተ አምጻእኩ ለብሔር፤ ወምንተ እፈቅድ፡ ዘእንበለ አንድዶታ!"** ማለትም፡ **"በምድር ላይ፡ እሳትን አምጥቻለሁ፤ እርሷን ከማንደድ በቀር፡ ምን እሻለሁ?"** ብሎ የተናገረላትና የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያን ፀሮች ኹሉ እየተመራመረች፡ ፍዳቸውን የምትከፍለው፡ ያች፡ እሳት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ መላውን ዓለም እያጥለቀለቀ የሚታየውን፡ ረቂቅ የነውጥና የለውጥ ነበልባላዊ ማዕበል፡ ኮስትራ አቀጣጠለችው! ነድላም ለቀቀችው! (መዝ. ፵፱፥ ፪-፫። ሉቃ. ፲፪፥ ፵፱።)

በዓለሙ ዘንድ እንደእንግዳ የታየው፥ ለኢትዮጵያ ልጆች ግን፡ አዲስ ያልኾነው፡ ይህ፡ ረቂቅ ትንቢታዊ ማዕበል፡ ለዓለማውያኑ እንደመሰላቸው፡ ሥጋዊ ብቻ አይደለም፤ ነፍሳዊና መንፈሳዊም ነው እንጂ። እንዲህ እንደመኾኑ፡ የሚያስከትለው ትንግርት፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታውያኑ ዘንድ ካልኾነ በቀር፡ በሰብአውያኑ አእምሮ፡ ሊደረስበትና ሊታወቅ ከቶ አይቻልም።

ይኸ የመለኮት እሳታዊ ማዕበል፡ ፍሕሙ ተተርኵሶ፥ ግድቡም ተነድሎ፡ ኹለንተናዊ የአንሰሓስሖ እና ማኅየዊ የአንጽሖ (የኹለመና መነሣሣት እና ሕይወትን የማጥዳት) እንቅስቃሴውን፡ በኢትዮጵያ፡ ማካኼድ የጀመረው፡ በጥቅምት ፲፰ ቀን፥ ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. በተሰማው፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ የምሥራች ነጋሪት ድምፅ ነው።

አዎን! ልክ፡ በዚሁ ወር፥ ቀንና ዓመተ ምሕረት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው ኢትዮጵያ፡ በቤተ ሕዝቧ፥ በቤተ ምልክናዋና በቤተ ክህነቷ፡ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ አቋማት ላይ፡ በመንፈስ ቅዱስ አሳሳቢነትና መሪነት ያዘጋጀችውን፡ የ<u>ሰበካ ጉባኤ ቃለ ዓዋዲ</u> በይፋ ዐወጀች።

ወዲያው፡ ይህ ቃለ ዓዋዲ ያሠረፀው፡ ያ መለኮታዊው የእሳት ማዕበል፡ ተቃዋሚዎቹን፡ በረቂቅ ነበልባሉ እየተከታተለ ማቃጠልና ማጋየት፥ ማጥለቅለቅና ማስወገድ ጀመረ።

በኀቡዕ ክህደቱና በሥውር አመንዝራነቱ፡ በቅዱሱ ኪዳኗ ላይ ሲያምፅ የኖረውን፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን ትውልድ፡ በማስቀደም፡ ይኸው መለኮታዊው የእሳት ማዕበል፡ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ፡ ፀረ-ኢትዮጵያ አህጉራትንና ሕዝቦችንም በማከታተል፡ በማይበገረው ኃይሉና ጽናቱ፡ እየለየ ሲያቃጥልና እያጥለቀልቀ ሲደመስስ ቆየ፤ አኹን ደግሞ፡ ተልእኮውን ሊያጠናቅቅ፡ እነሆ፡ ፍጥረተ ዓለሙን ኹሉ፡ አንድ በአንድ፡ በተራ በማዳረስ፡ እየጋመና እያስገመገመ ሲኼድ ይታያል።

\+ \+ \+

ለመኾኑ፡ ይህን እያስደረገች ያለችው፡ ይህች "ኢትዮጵያ" ማናት?

እርሷማ፡ በፍጥረት ልደት፡ የዛሬ ፯ሺ፭፻፫ ዓመታት፡ በአዳምና ሔዋን ህልውና ተዘርታ የበቀለችው፡ የእግዚአብሔር አገርና መንግሥት፥ የቃል ኪዳን ሕዝቡ መኖርያና የዓለሙ መፈረጃም የኾነችው ናት!

በመካከሉም፡ የእኒሁ፡ የሰው ዘር ግንዶች፡ ደጋግ ልጆች በኾኑት፡ ኖኅንና መልከ ጼዴቅን፥ አብርሃምንና ሙሴን፥ እንዲሁም ዳዊትን በመሰሉት፡ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳናውያን፡ እውነተኛ ሃይማኖትና የታማኝነት ምግባር፡ ለ፭ሺ፭፻ ዓመታት ስትለመልም የቆየችው ናት!

በዘመኑ መጨረሻም፡ የዛሬ ፪ሺ፫ ዓመታት፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ለዘለዓለማዊው የሕይወት ፍሬ የበቃችው ናት።

\+ \+ \+

"ኢትዮጵያዊ ነኝ!" በሚለውና በመላው ዓለም የምድር ገጽ ላይ በሚርመሰመሰው፡ በዛሬው "የሰው ዘር" አጠቃላይ ትውልድ ላይ እየደረሰ ያለው፡ ይህ፡ አጥለቅላቂና ደምሳሽ ኹኔታ፡ ከዚያ፡ ከመለኮታዊው የእሳት ማዕበል ፊት ቀድሞ ሊካኼድ የሚያስፈልግ መኾኑን የሚያመላክተው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ እዚህ ላይ ሊወሳና ሊዘከር ይገባል፤ እርሱም፡ በዘለዓለማዊው መሪያችንና በአምላካዊው መምህራችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የትስብእት አንደበት፥ ኋላም፡ በመንፈስ ቅዱስ የተነገረው፡ እንዲህ የሚለው ነው፡-

፩ኛ፡ "ዑቁ ኢያስሕቱክሙ፤ እስመ ብዙኃን ይመጽኡ በስምየ፡ እንዘ ይብሉ፡- 'አነ ውእቱ ክርስቶስ!' ወያስሕትዎሙ ለብዙኃን። ወአመ ሰማዕክሙ ቀትለ፥ ወድምፀ ፀባኢት፡ ዑቁ! ኢትደንግፁ! እስመ ግብር ይከውን ዝንቱ፤ ወባሕቱ፡ አኮ በጊዜሃ ዘየኀልቅ። ወይትነሥኡ ሕዝብ ዲበ ሕዝብ፤ ወነገሥት ላዕለ ነገሥት፤ ወይመጽእ ረኃብ፥ ወብድብድ፥ ወድልቅልቅ፥ ወሀከክ፡ በበብሔሩ። ወዝንቱ ኵሉ ቀዳሚሁ ለሕማም።

"...ወአሜሃ፡ የዐልዉ ብዙኃን ሃይማኖቶሙ፤ ወይጻልኡ በበይናቲሆሙ፤ ወይትቃተሉ። ...ወእምብዝኀ ዓመፃ፥ ወእከይ፡ ትሴኵስ ፍቅር እምብዙኃን፤ ወብዙኃን፡ የዓልዉ ሃይማኖቶሙ ወፍቅሮሙ። ወዘሰ አዝለፈ ትዕግሥቶ፡ ውእቱ ይድኅን።

"ወይሰበክ ዝ፡ ወንጌለ መንግሥት፡ ውስተ ኵሉ ዓለም፡ ከመ ይኩን ስምዐ ላዕለ ኵሉ አሕዛብ። ወይእተ አሚረ፡ ይበጽሕ ኅልቀት።

"...ወበከመ ኮነ፡ በመዋዕለ ኖኅ፡ ከማሁ ይከውን ምጽአቱ፡ ለወልደ እጓለ እመሕያው። እስመ በከመ ኮነ፡ በመዋዕለ ኖኅ፡ እምቅድመ ማየ አይኅ፡ ይበልዑ፥ ወይሰትዩ፥ ወያውስቡ፥ ወይትዋሰቡ፡ እስከ አመ ቦአ ኖኅ ውስተ ታቦት፤ ወኢያእመሩ፡ እስከ አመ መጽአ ማየ አይኅ፤ ወአጥፍአ ኵሎ። ከማሁኬ፡ ይከውን ምጽአቱ፡ ለወልደ እጓለ እመሕያው።"

፩ኛ፡ "ወሶበ ኀልቀ ፲፻ ዓመት፡ ይትፈታሕ ሰይጣን እምነ ሞቅሑ። ወይወፅእ ያስሕቶሙ ለአሕዛብ፡ እለ ውስተ አርባዕቱ መአዝኒሃ ለምድር፤ ወያስተጋብአሙ፡ ለጎግ ወለማጎግ፡ ከመ ያስተቃትሎሙ፤ ወኍልቆሙሰ፡ ከመ ኆጻ ባሕር። ወዐርጉ ውስተ ስፍሓ ለምድር፤ ወዐገትዋ ለትእይንቶሙ ለቅዱሳን፥ ወለሀገር ቅድስት። ወእምዝ ወረደት እሳት እምሰማይ፡ እምኀበ እግዚአብሔር፤ ወበልዐቶሙ። ወለዝኩቱኒ ሰይጣን፡ ዘያስሕቶሙ፡ ወደይዎ ውስተ ዐዘቅተ እሳት፥ ወተይ፡ ኀበ ሀሎ ዝክቱ አርዌ፥ ወሓሳዌ ነቢይ፡ ከመ ይደየኑ፡ መዐልተ ወሌሊተ፡ እስከ ለዓለመ ዓለም።"

ይህም ማለት፡ ፩ኛ፡ "ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ! ብዙዎች፡ 'እኔ ክርስቶስ ነኝ!' እያሉ፡ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም፡ ያስታሉ።

"ጦርንም፥ የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ። ይህ ሊኾን፡ ግድ ነውና፡ ተጠበቁ! አትደንግጡ! ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው። [አስቀድሞ] ሕዝብ በሕዝብ ላይ፥ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና። ራብም፥ ቸነፈርም፥ የምድር መናወጥም፡ በልዩ ልዩ ሥፍራ ይኾናል። እኒህ ኹሉ፡ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።

"...በዚያን ጊዜም፡ ብዙዎች፡ ሃይማኖታቸውን ይክዳሉ፤ እርስ በርሳቸውም፡ አሳልፈው ይሰጣጣሉ፤ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ፤ ይጋደሉማል። ...ከዓመፃም ብዛት የተነሣ፡ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች፤ ብዙዎች፡ ሃይማኖታቸውንና ፍቅራቸውን በመካድ፡ ይሰነካከላሉ። <u>እስከመጨረሻው የሚጸና ግን፡ እርሱ ይድናል።</u> ለአሕዛብም ኹሉ ምስክር እንዲኾን፡ ይህ የመንግሥት ምሥራች፡ በዓለም ኹሉ ይሰበካል። በዚያን ጊዜም፡ መጨረሻው ይመጣል።

"...የኖኅ ዘመን እንደነበረ፡ የሰው ልጅ መምጣት፡ እንዲሁ ይኾናልና።

"በዚያች ወራት፡ ከጥፋት ውኃ በፊት፡ ኖኅ ወደመርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፡ ሲበሉና ሲጠጡ፥ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደነበሩ፥ የጥፋት ውኃም መጥቶ፡ ኹሉን እስከወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፡ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ፡ እንዲሁ ይኾናል!"

፪ኛ፡ "ሺሁም ዓመት ሲፈጸም፡ ሰይጣን ከእሥራቱ ይፈታታል። በአራቱም፡ በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ፡ ጎግንና ማጎግን እንዲያስታቸው፥ ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው፡ ይወጣል፤ ቍጥራቸውም፡ እንደባሕር አሸዋ የሚያህል ነው። ወደምድርም ስፋት ወጡ፤ የቅዱሳንንም ሠፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ። እሳትም፡ ከሰማይ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው። ያሳታቸውም ዲያብሎስ፡ አውሬውና ሓሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት፡ ወደእሳቱና ወደዲኑ ባሕር ተጣለ! ለዘለዓለምም፥ እስከዘለዓለም፡ ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ።" (ማቴ. ፳፬፥ ፫-፲፬፤ ፴፯-፴፱። ራእ. ፳፥ ፯-፲።)

ከዚህ በላይ የተጠቀሰውና የማይታበለው የእግዚአብሔር ቃል፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የሚያረጋግጥላቸው፡ አንድ ፍጹም እውነታ አለ፤ እርሱንም፡ በሃይማኖታዊው የእውቀት ዓይናቸውና የኹለንተና አእምሮአቸው ሊያዩትና ሊመለከቱት፥ ሊያስተውሉትና ሊገነዘቡት ይገባቸዋል።

ይህም እውነታ፡ በዛሬው "የሰው ዘር" አጠቃላይ ትውልድ ላይ እየደረሰ ያለው፡ ይህ፡ አጥለቅላቂና ደምሳሽ ኹኔታ፡ "ወረደት እሳት እምሰማይ፡ እምኀበ እግዚአብሔር፤ ወበልዐቶሙ!" ማለትም፡ "እሳትም፡ ከሰማይ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው።" ከተባለችው፡ ከዚያች፡ ከመለኮታዊዋ የእሳት ማዕበል ፊት፡ ቀድሞ ሊካኼድ የሚያስፈልግ የመኾኑ እውነታ ነው።

+ + +

እንግዴህ፡ እውነተኞች የኢትዮጵያ ምእመናንና ካህናት፡ ቀደም ብሎ በተወሳው፡ በሰበካ ጉባኤ ቃለ ዓዋዲ የተከሠተው፡ ይህ ዓይነቱ፡ ጥንታዊ የእግዚአብሔር ሥርዓት መኖሩን ሊያውቁ፥ አውቀውም፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው ተማምነውና በንስሓ ምግባራቸው ነጽተው፥ ተግባብተውና ተስማምተው፥ ተባብረውና ተጠናክረው፡ ሊገለገሉበትና ሊያገለግሉበት ይጠበቅባቸዋል። እርሱም፡ በአገር ውስጥና በውጪ ባሉ አህጉር፡ የሰበካ ቤተ ክርስቲያንን በማደራጀትና በማቋቋም፥ በማስተዳደርና በማካኼድ፡ በዚሁ የኢትዮጵያዊነት ማንነታቸው፡ እየራሳቸውን በግልጽ አሳውቀው፡ በቀናው መንገድ፡ በተግባር ላይ ሊያውሉት የሚችሉበት ሥርዓት ነው።

ምናልባት ግን፡ ይህን እውነታ ባለማወቅ፥ ወይም፡ አውቀውት፡ ሊሠሩበት ባለመፈለግ ብቻ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በያለበት፡ እጅግ አሳሳቢና አሳዛኝ የኾነውን ጠንቀኛ ችግር፡ በየራሳቸው ላይ እየፈጠሩና እያደረሱ የሚሠቃዩ፥ ኅብረተሰባቸውንም የሚያውኩ አላዋቂዎች ካህናትና ምእመናን ቢኖሩ፡ ለዚህ ችግራቸው፡ ብቸኛው መፍትሔ የሚኾናቸው፡ ከዚችው፡ ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የተሰጠው፡ ይኸው፡ እውነተኛውና ትክክለኛው የሰበካ ጉባኤ ቃለ አዋዲ መኾኑን ሊገነዘቡት ይገባቸዋል።

ይህንኑ ቃለ ዓዋዲ፡ በታመነ እውነተኛ አገልግሎት ላይ ዐውላችሁ፡ ለጣፋጩ የሕይወት ፍሬ ታበቁት ዘንድ፡ ከአብነቱ ዕትምና ከሥነ ጽሑፍ ዝግጅቱ፥ ከመምሪያ ሓተታውና ከማብራሪያ ጓዙ ጋር፡ ይኸው ቀርቦላችኋል።

---

በአንድ ሰብኣዊ አካል ውስጥ፡ ነፍስና ሥጋ፡ በመንፈስ፡ አንድ ኾነው፡ በተዋሕዶ የሚገኙበት ካልኾነ በቀር፡ ያ አካል፡ "ፍጹም ሕያው ሰው ነው!" ተብሎ፡ በሕይወት ሊንቀሳቀስና ሊሠራ እንደማይችል፡ በማንም ዘንድ፡ በይፋና በገሃድ የሚታወቅ እውነታ ነው።

ይህም፡ "ነፍስና ሥጋ፡ በመንፈስ አንድ መኾናቸው ቀርቶ፡ የተለያዩ ኾነው ለመገኘት ቢሞክሩ፡ ውጤቱ ምን ዓይነት እንደሚኾን፡ የታወቀ ነው፡- ነፍስ የሌለው የሥጋ አካል፡ በግዝፈቱ ምክንያት፡ በድን ኾኖ 'ሬሳ' ይባላል፤ ነፍስም፡ ከረቂቅነት ባሕርይዋ የተነሣ፡ ያን፡ ገዝፋ የተገለጠችበትን አካል በማጣቷ፡ ለብቻዋ ልትታይና ልትዳሰስ አይቻላትምና፡ 'ሥውር' ትኾናለች!" ማለት ነው።

ስለዚህ፡ ሰው፡ በዚህ ዓለም፡ ሕያው ኾኖ፡ በመልካም ሊኖርና ሊንቀሳቀስ፥ ሊያስብና ሊሠራ ይችል ዘንድ፡ ነፍሱ፡ ሙሉና ጤናማ ከኾነ ሥጋ ጋር፡ በመንፈስ ተዋሕዳ ልትገለጥ ያስፈልጋታል።

እንዲሁ ኹሉ፡ አንድ አገር፡ እንደነፍስ ለሚቆጠረው ለቤተ ሕዝቡ አካልና ባሕርይ፡ ኹለቱ አካላትና ባሕርያት ሊኖሩት ይገባል። እነዚህም፡ በአንድ በኩል፡ በሥጋዊ ህልውናው ረገድ፡ አካላዊ ግዝፈትንና የኑሮ አገልግሎትን የሚሰጠው፡ የቤተ ምልክና አቋም የሚያስፈልገው ሲኾን፥ በሌላው በኩል ደግሞ፡ በመንፈሳዊ ህልውናው ረገድ፡ ሕይወታዊ ባሕርይንና ሃይማኖታዊ አገልግሎትን የሚያበረክትለት፡ የቤተ ክህነት ዘርፍ እንዲኖረው ያስፈልጋል።

እንዲህ ካልኾነ፡ ያ አገር፡ ከግለሰብና ከቤተሰብ፥ ከኅብረተሰብና ከብሔረሰብ አንሥቶ፥ ከዚያም አልፎ፡ በሕዝብነት ስፋት ተደራጅቶ ሊኖርና ሊሠራ ከቶ አይቻለውም። ያንን፡ ዘመን አመጣሹንና የባዕዳን የኾነውን፡ ሰብአዊ ፍልስፍና፡ ስሕተትና ውድቅ የሚያደርገው፡ ይኸው፡ ከላይ የተብራራው፡ የእግዚአብሔር የኾነው የሥነ ፍጥረት እውነታ ነው።

"ዘመን አመጣሹና የባዕዳን የኾነው፡ ሰብአዊ ፍልስፍና" የሚባለውም፡ "መንግሥት" የሚል መጠሪያ ተሰጥቶት፡ የአንድን አገር ሕዝብ ሥጋዊ ህልውና፡ በሠይፍ ሥልጣን የሚገዛው፡ የቤተ ምልክናው አካል እና ለዚያ ሕዝብ፡ መንፈሳዊ ህልውና መገለጫ ኾኖ፡ ሃይማኖታዊ አገልግሎትን የሚያቀርበው፡ የቤተ ክህነቱ ዘርፍ፡ ተለያይተው እንጂ፡ አንድነት ኾነው ሊሠሩ አይችሉም!" የሚለው ዘዬ ነው።

ከላይ፡ ቀደም ብሎ በአርእስቱና በተከታዩ አንቀጽ የተገለጸውን፡ መለኮታዊ፡ የእውነት ሥርዓት ጠብቃ፥ በእርሱም ተጠብቃ በኖረችው፡ በአገራችን በኢትዮጵያ፡ ጥንታዊና ረዥም በኾነው፡ በቅዱሱ ኪዳን ህልውናዋ መዋዕል ውስጥ፡ የእግዚአብሔር የኾነ፡ አንድ ልዩ አዋጅ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ በአዲስ አበባ፥ በወረቀት ሰሌዳ ተጽፎና ታትሞ መውጣቱ፥ በሥራ ላይ ውሎም፡ ለፍሬ መብቃቱ ይታወሳል። ያም፡ "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቃለ ዓዋዲ" በሚል አርእስት፡ በጥቅምት ፲፰ ቀን፥ ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. የታወጀው ነው።

ይህ አዋጅ፡ እንደመለኮታዊው ትንቢት፡ ለዝንተ ዓለም፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የልብ ጽላት ላይ፡ በመለኮታውያኑ ጣቶች ተጽፎና በየልቦናቸው አድሮ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው፡ በእናት አገራቸው፡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ አቋም አማካይነት፡ ሥጋዊዉን አገልግሎት ከሚሰጠው፡ ከቤተ ምልክናቸው ጋር፡ መንፈሳዊዉን አገልግሎት የሚያበረክተውን ቤተ ክህነታቸውን ሲመሩበትና ሲያስተዳድሩበት፥ ሲገለገሉበትና ሲያገለግሉበት የኖረው ሥርዓት ነው።

ይኹን እንጂ፡ ይህን የመሰለ፡ ፍቱን የኾነ መልካም የፍቅር መሣሪያ እያለ፡ እየራሳቸውን፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" ብለው በሚጠሩት፡ በአገርም ውስጥ ኾነ፥ በተለይ፡ ከአገር ውጭ ተበትነው ባሉት፡ በቤተ ክህነቱ፡ ምእመናንና ካህናት መካከል፡ የመለያየትና የመቃቃር፥ የክርክርና የፀብ ኹኔታ፡ ሲካኼድ ማየቱ በእርግጥ ያሳዝናል።

እነሆ፡ መላው ዓለም፡ በገሃድ እያየ፡ "ሊቃነ ካህናት (ጳጳሳት)" በተባሉት በቀንደኞቹ መነኮሳት ፊታውራሪነት፡ የሚካኼደውን አሳዛኝ ኹኔታ፡ ምንነቱን ገላልጠን በማወቅ፡ እስኪ አኹን፡ እኛም፡ ለጥቂት አፍታ እንመልከተው!

ይኸው አሳዛኙ ኹኔታ የተፈጠረው፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ለአገሩ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት ሊውሉ የሚገባቸውን፡ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ክህነቱንና ቤተ ምልክናውን፡ በአንድነት በማስተባበር፡ ከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ፡ በፈጣሪው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ቅዱስ ኪዳን ላይ፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአመንዝራነት ኃጢአትን፡ በይፋ በመፈጸሙ ያስከተለው ጠንቅ መኾኑ፡ በግልጽ ታውቋል።

ከዚህ ጠንቅ የተነሣ፡ እንደመለኮታዊው የፍርድ ቃል፡ "በልቅሶና ጥርስ በማፋጨት" ቍጭት ጭምር እየተሠቃየ የቀጠለውን፡ የቤተ ሕዝቡንና የቤተ ምልክናውን ጽዋ፡ ለጊዜው ተወት አድርገን፡ የቤተ ክህነቱን ዕድል ፈንታ፥ በተለይ፡ በባሕር ማዶ ተበታትኖ የሚናውዘውን ስንመለከተው፡ የባሰ መራራ ኾኖ እናገኘዋለን።

ይኸውም፡ "ሊቃነ ካህናት ነን!" በሚሉት፡ "ጳጳሳት" በሚባሉት መነኮሳት ቀስቃሽነትና መሪነት፡ በካህናቱና በካህናቱ፥ በካህናቱና በምእመናኑ፥ በምእመናኑና በምእመናኑ መካከል እየተፈጠረ የሚካኼደው ከፍተኛ አለመግባባትና የተካረረ ክርክር፥ የከፋ ጥላቻና ሥር የሰደደ ፀብ ነው። በዚህ ምክንያት፡ እርስ በእርሳቸው በመካሰስና ባዕዳን ጠበቆችን፡ በሌለ ገንዘባቸው እያቆሙ፡ ያለኀፍረትና ይሉኝታ፡ በየዓለማውያኑ ፍርድ ቤቶች በመጓተት፡ የሃይማኖት ተፃራሪዎቻቸው መሣቂያና መሳለቂያ፥ መዘበቻና መዘባበቻ ኾነው እስከመታየት ያደረሰውን፡ ጸያፍና አረማዊ ድርጊታቸውን በየጊዜውና በየቦታው ማየቱና መስማቱ አሰልቺ እየኾነ መኼዱ፡ ሊታበል ከቶ አይቻልም።

ስለዚህ፡ ቅን ልቡናና ትሑት ሰብእና ያላችሁ፥ "በእውነት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" የምትሉ፥ ከካህናቱም ኾነ፥ ከምእመናኑ ወገን፡ ለዐዋይ የቀራችሁ፡ ምናልባት፡ ጥቂቶች ካላችሁ፡ ይህን፡ የኢትዮጵያን መለኮታዊ መልእክት ይዘንላችሁ ቀርበናል።

አዎን! የእግዚአብሔር እውነት የኾነው መንፈስ ቅዱስ አድሮባችሁ፡ መልካሙን ልታደርጉበትና ጣፋጩን የንስሓ ፍሬ ልታስገኙበት ይቻላችሁ ዘንድ፡ በመልካም ዘርነቱና ፍሬያማነቱ የታወቀውንና የተረጋገጠለትን፡ ይህን እውነተኛና ትክክለኛ፡ የሰበካ ጉባኤ ደንብ፡ ከመመሪያውና ከማብራሪያው ጋር፡ ኢትዮጵያኛውን ብቻ ሳይኾን፡ እንግሊዝኛውንም፡ በዚህ የጎዋ ሰሌዳችን ላይ እንደገና ዐትመን አውጥተንላችኋል።

እንደገና ያልነው፡ ያለምክንያት አይደለም፤ ቀደም ብለው፡ ከዓመታት በፊት በታተሙትና በተሠራጩት፥ በጎዋ ሰሌዳችንም ላይ ተዘርዝረው በቀረቡት መጽሓፎቻችን፥ በተለይም፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" እና "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት! ፫ኛ መጽሓፍ" ውስጥ፡ ይኸው ቃለ አዋዲ ተመዝግቦ ስለሚገኝ ነው።

እነዚህኑ መጻሕፍት፡ እስካኹን፡ ጠይቃችሁና ፈልጋችሁ በማግኘት፡ የዚህን የአዋጅ ቃል፡ ዝርዝር ሓተታና መመሪያ በሚመለከት፡ የተሟላ እውቀትን አትርፋችሁበት፡ ልትጠቀሙበት ሳትችሉ እንዳልቀራችሁ እናምናለን።

አኹንና እንግዴህ ወዲህም፡ በፈጣሪያችሁ ላይ መታመኑና ተነሳሒነቱ፥ አምልኮቱና ፍላጎቱ ኖርዋችሁ፡ በየበኩላችሁ፡ በእውነትና በታማኝነት፡ በተግባር ላይ ልታውሉት የምትፈቅዱ ከኾናችሁ፡ በመካከላችሁ የተፈጠረውን አለመግባባት አስወግዶ፡ ሊያስማማችሁ፥ በበለጠ አስተባብሮም ሊያጠናክራችሁ፥ በየፍርድ ቤቶች የተከፈተ ክስና በቀጠሮ ላይ የሚገኝ ክርክር ካለም፡ ለዳኞቹ እያቀረባችሁ፡ መዝገባችሁን ልታዝዘጉበት፥ ምናልባትም፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሥርዓት መሠረት፡ አዲስ ሰበካ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም የምትሹ ካላችሁ ደግሞ፡ አመሠራረቱንና አስተዳደሩን አውቃችሁ፡ ተገቢውን ለመፈጸም የሚቻላችሁ ይኾናል።

ይህ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት በኩል፡ ዛሬ የቀረበላችሁ፡ የሰበካ ጉባኤ ቃለ አዋዲ፡ "እግዚአብሔር የለም!" ይል በነበረው፡ በደርግ አዛዥነትና ተቆጣጣሪነት፥ የእርሱ ታማኞች በኾኑት፡ በዘመኑና ዛሬም ባሉት፡ የቤተ ክህነቱ አመራር ባለሥልጣኖች መነኮሳት ተባባሪነት፡ ለእነርሱ የግል ሥልጣንና ጥቅም ሲሉ ለዋውጠው ያማሰኑትን፥ አኹንም፡ በአገር ውስጥ ያሉትም ኾኑ፡ በውጭው አህጉር የሚኖሩት፡ እየሠሩበት ያለውን፡ "ሓሳዊ" የሰበካ ጉባኤ ደንብ አለመኾኑ እንዲታወቅ ያስፈልጋል።

ከላይ፡ በአርእስቱ በተገለጸው ዘመን፡ ማለትም፡ በጥቅምት ፲፰ ቀን፥ ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. በኢትዮጵያኛ እና በእንግሊዝኛ ተዘጋጅቶና ወጥቶ ይሠራበት የነበረውን፡ የሰበካ ጉባኤ ቃለ ዓዋዲ፡ ብርሃናዊ ቅጂ፡ በዕትም ቅጹና በዛሬው የሥነ ጽሑፍ መልኩ፡ ከመመሪያውና ማብራሪያው፥ እንዲሁም፡ ከመነሻ ዓላማውና መድረሻ ግቡ "ሰፊ ሓተታ" ጋር፡ በዚህ መልእክት ሸኝነት፡ አሟልተን አቅርበንላችኋልና፡ አንድ በአንድ ትመለከቱት ዘንድ ስንጋብዛችሁ፡ በውጤቱ እንደምትረኩ በማመን ነው።

\+ \+ \+